**ጥቅምት 2005 ዓ.ም.**

## <u>አሳሳቢውን የትምህርት ስርዓት ዝቅጠት በኢሮብ ወረዳ ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?</u>

## ክፍል አራት፣

## <u>Irob Scholarship & Education Support Program (ISESP) ወደየትእየሄደ ነው!</u>

በኢሮብ ወረዳ ዛሬ ሰፍኖ ያለውን የትምህርት ስርዓት ዝቅጠትን ለመቅረፍ/ለማሻሻል እንደ ዜጎች ምን ማድረግ አለብን በሚለው አጀንዳ ሁሉንም ያሳተፈ ውይይት እንዲቀጥል በማለት በራሴ በኩል የሚታዩኝ የመፍትሄ ሃሳቦች ሳላካትት የተለያዩ ለውይይት ጋባዥ ጥያቄዎችን በማንሳት፣ መሰረታዊ ችግሮች ናቸው ያልኩዋቸውን በመጠቆም ሶስት ተከታታይ መጣጥፎች ማቅረቤ የሚታወስ ነው። ለዚህ ተከታታይ መጣጥፌ መነሻ የሆነኝ ከፕሮግራሙ መስራቾች አንዱ የሆኑት አቶ ዚያደ ኃይሉ በኢሮብ ወረዳ ዛሬ ሰፍኖ ያለው የትምህርት ዝቅጠት በትክክል አመላካች የሆነው አጭር ግን በጣም አስደንጋጭ መልእክትና Irob Scholarship and Educational Support Program (ከንግዲህም በአህጽሮቱ ISESP እያልኩ የምቀጥለው)፣ በ2011 ሲመሰረት መስረታዊ ዓላመዬ/objectives በማለት ያስቀመጡት ነበር።

የመጣጥፎቼ መነሻና መድረሻን ለመከታተል እንዲያመች መነሻዬ የነበሩትን የአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር መልእክትና የISESP ሲመሰረት ይዞት የተነሳው መሰረታዊ ዓላማ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

### I. የአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር መልእክት፣

**"Analyze this: For starters here is the report card on Irob education according to the Woreda chief: out of 300 students who sat for 10th grade exams only 39 merely passed. And out of those 39 who participated in preparatory (12th) exams only 7 passed with no particular flying colors. And only God knows how those 7 succeed in completing the university degree. Besides school drop rate is hovering between 30%-50% - go figure out people…"** ።

### II. <u>SESP ሲመሰረት ይዞት የተነሳው መሰረታዊ ዓላማ/objectives</u>

**"3. Project Description**

**3.1 General Objective**

The project aims to provide scholarship opportunities to academically qualified, those who demonstrate leadership qualities but financially needy students by providing them financial assistance.

**3.2 Specific Objectives**

**The proposed project will attain the following specific objectives in the project duration**

- To cover basic college needs of 12 students for the period of four years. i.e., Provision of support for purchase of text books, feminine hygiene products, clothes and pocket money; covering costs related to stationery and photocopy costs; covering transportation cost from Irob *woreda* to University location and back.

- To engage scholarship wining students to provide free teaching services in assigned *woreda* schools in their free time.

- To Strengthen and promote volunteerism in Irob community

**3.3 Expected out puts and outcomes**

- 12 competent and needy students are graduated from universities with skills and knowledge that helps them contribute to the community.
- 12 competent and needy students become economically self sufficient
- The graduating students become role models for other students
- Capacity of local schools is enhanced with support from scholarship winning students
- Volunteerism and sense of community is promoted”

## III. ለISESP ዓላማ በወቅቱ የኢሮቦች መልስ ምን ነበር?

ምንም እንኳን ISESP ሲመሰረት ይዞት የተነሳው ዓላማ በኢሮብ ወረዳ ሰፍኖ የሚታየውን  ዘርፈ ብዙ የትምህርት ተቋም ችግሮች የማይፈታ መሆኑ ከጅምሩ ይታወቅ የነበር ቢሆንም፣ ምንም ካለማድረግ ጥቂቶቹንም ቢሆን ለመርዳት የሚያስችል ዓላማ አንግቦ የተወሰኑ ወጣቶችን ለቁምነገር ለማድረስ የሚደረገው ጥረት መታገዝ አለበት በማለት፣ ይህን በጎ ጅማሮን እንደ መነሻ በመጠቀም በሁሉም ወገን ከተሰራበት አጠቃላይ የኢሮብ ወረዳ ዘርፈ ብዙ የትምህርት ተቋም ችግሮች በጋራ ታግሎ ለመቅረፍ ወደሚደረገው የጋራ እንቅስቃሴና አንድ ሁሉንም ኢሮቦች አቀፍ ማህበር ወደ መመስረት ሊያደርሰን ይችላል በሚል ቅን ሂልናና መንፈስ በመነሳሳት በወቅቱ በርካታ አገር ቤትም ሆነ በባሕር ማዶ ነዋሪ የኢሮብ ተወላጆች ዓላማውን ከልብ ደግፈውታል፣ ይህን ድጋፋቸውንም በየአከባቢው በራስ አነሳሽነት ባጭር ጊዜ ውስጥ ባደረጉት የገንዘብ ማሳባሰብና ዓዲግራት/ትግራይ ለዚህ ጉዳይ በከፈተው ISESP አካውንት ፈጥኖ በመላክ አስመስክሯል።

## IV. <u>ከአንድ ዓመት በኋላስ የISESP ዓላማ ምን ይመስላል?</u>

የISESP አመራር በጁላይ 2012 ላይ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከሚኖሩ ኢሮቦች የተሰበሰበው ገንዘብ እንዴት እንዳከፋፈለው የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት በኢሮብ ኦርግ ድረገጽና በጎሮን ፈይስቡክ ፎረም በኩል ተልኮ ሁላችን ተመልክተነዋል። ለዝርዝሩ (IDA-ISESP)Yearly Progress Report for the year 2012(2004E.C) ርእስ ስር የተዘረዘረውን መመልከት ይቻላል።

በዚህ ዓመታዊ ሪፖርቱ ISESP መሰረታዊ ዓላማውን እንደሚከተለው አስቀምጧል።

እጠቅሳለሁ፣

### “2. General and specific objectives of the ISESP

### 2. 1 General Objective

- It is to promote and support educational excellence and advancement of Irobs at different levels and combat poverty.

“3. Yearly planed activities Vs achievement of the program

### 3.1 In primary and secondary high schools

- Focusing on grade 5-12 the program planed to motivate learning appetite of students, through giving recognition to competent candidates who stood 1st -3rd in their class and have average points strictly above **90** points. The plan the program articulated was to give **60** (top sixty) students rewards (1 dictionary, **12** exercise books, and **48** pens that was expected to help for **one** year for school materials), roughly this costs **598.00 Birr**. Based up on the needs in the ground and requests from the administration and education office the program also planned to financially support **20** needy students with **2,000.00Birr. This** financial support was expected to help them to cover their house rent during school time.
- Accordingly top **60** students and **20** needy students received the financial support according to the plan. For this propose **75,880.00** Birr was utilized. "

### 3.2 Scholarship for undergraduate programs level

- The program planed to motivate learning appetite of irob students in public universities in ethiopia on regular programs through giving recognition and monthly financial support to competent candidates. Accordingly this year plan will accommodate ten **(10)** top students attending their studies in universities in 1st degree level and similarly to encourage girls/ female students; in this year 2012 five **(5)** top female students attending their studies in universities in 1st degree level will get monthly **300.00Birr** financial support. The transfer of money will be directly to their individual bank account. Note: A probability for top female students to get two rewards at the same time is possible (Which is one of the ten top and one from five top female students). This was planed
- Regarding the scholarship for undergraduate levels, it is on the process of selecting 15 top students across the public universities in the country. Therefore as soon as all the tasks accomplished it will be reported to the public. For this propose **54,000.00**Birr is expected to be utilized in the coming months. So due to this fact that the grade reports are not in our hands, it was not possible to implement it in time. We hope to obtain their results in few weeks time".

እኔ ከላይ የተቀመጠውን የISESP ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ የሰፈረው ዓላማ ከተመለከትኩ በኋላ ISESP ወዴት እየሄደ ነው የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት ተገድጃለሁ። የሙያው ጠበብት የISESPን አካሄድ እስመልክቶ አቅጣጫ ያመላክቱ በሚል በተስፋ ስጠባበቅ ብቆይም ዘላቂ መፍትሔ ጠቋሚ የሚያረካ ትንተና የቀረበ እስካሁን አላነበብኩም። ለኔ የትምህርት ዘርፉ ሂደት የተዘፈቀበት ቀውስ፣ የISESP የመፍትሔ ሓሳቦችና የቅድሚያ አመራረጥ የተጣጣሙ አልመሰሉኝም። ስለሆነም በበኩሌ በዚህ ISESP ባቀረበልን ዓመታዊ ሪፖርት ዓላማ ላይ የሚታዩኝ አንዳንድ የአሰራርና የቅድሚያ አሰጣጥ ጉድለቶች አሉባቸው ብዬ ባሰብኩዋቸው ነጥቦች ላይ ግድፈቶች ናቸው ያልኩዋቸውን በማስቀመጥ፣ በኔ በኩል የሚታዩኝ የመፍትሔ ሓሳቦችንና ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ያልኩዋቸው ችግሮች ለማስቀመጥ እሞክራለሁ። ይህን የማደርገው ደግሞ ISESP የጀመረው ጅማሮ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስ፣ ግድፈቶች በወቅቱ ተጠቁመው ISESPና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተን ወገኖች አስፈላጊ እርምት በጊዜው እንድናደርግበት ይረዳል ከሚል ምኞትና ተስፋ በመነሳት ነው።

አሁን በቀጥታ ግድፈቶች ናቸው የምላቸውን ነጥቦች ከማስቀመጤ በፊት ISESP ሲመሰረት ይዞት የተነሳውን ዓላማ ለምን የተገደበ/conditional ድጋፌን እንደሰጠሁ ግልጽ ላድርግ። ሁላችን እንደምናውቀው ISESP ሲመሰረት ይዞት የተነሳው ዓላማ አንድና ግልጽ ነበር። እሱም፣ ተምረው ራሳቸውንና ማህበረሰባቸውን ሊጠቅሙ የሚችሉ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጥሩ ነጥብ ያጠናቀቁ ግን በድህነት ምክንያት የዩኒቨርስቲ ትምህረታቸውን ለመቀጠል ያልቻሉ 12 የኢሮብ ወጣቶችን ለ4 ዓመት ለዩኒቨርሰቲ ትምህረታቸው የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለመሸፈን የሁሉም ኢሮቦች ትብብር የሚጠይቅ ነበር። ISESP ሲመሰረት ይህን ዓላማ ከግቡ ለማደረስ የሚያስፈልገው

የገንዘብ መጠንም 132.192.00 (አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ፣ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት) ብር እንደሚሆን በግልጽ አስቀመጠ ነበር። እኔም ሆንኩ በርካታ ኢሮቦች የደገፍነውና ገንዘብ ያዋጣንለትም ለዚህ ግልጽና አንድ ዓላማ ነው የነበረው። ከዚህ ውጭ ለወደፊቱ ይህን በጎ ጅማሮ ወደላቀና ዘለቄታ ወደ አለው ሁሉንም ኢሮብ ያቀፈ ጠንካራ ማህበር ለመመስረት ውይይቱ ይቀጥላል የሚል እምነትና ተስፋን በመሰነቅ ነበር ISESPን የደገፍኩት። ግን አሁን ISESP ይህን የመጀመሪያ ዓላማውን የቀየረበት፣ የአሰራርና የቅድሚያ አሰጣጥ መጀመርያ የተቀመጠው ንድፍን ተከትሎ እየተፈጸመ እንዳልሆነ ሆኖ ታይቶኛል ።

## V. የISESP መሰረታዊ የአሰራርና የቅድሚያ አሰጣጥ ግድፈቶች የተኞቹ ናቸው?

### ሀ. የአሰራር ግድፈት

በመርህ ደረጃ በአመራርና በተመሪዎች መካከል ጥሩ የሆነ ግኑኝነትና እምነት እንዲኖር አመራሩ የሚሰራው ስራ፣ የሚያወጣቸው ዕቅዶች ለተመሪዎችም ለለጋሾችም ግልጽ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም አመራሩ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ አንድ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት እንዳስፈላጊነቱ ተመሪዎችን ማሳተፍ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ መርህ መሰረት የISESP አመራር አሰራርን ስመለከት አመራሩ ገና ከጅምሩ ለተመሪዎች ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና አሳታፊነት የጎደለው አሰራር እየተከተለ እንደሆነ ሆኖ ይሰማኛል።

ይህን በግልጽ ለማየት የISESP ዓመታዊ ሪፖርት ላይ የተቀመጠው ዓላማውና ዕቅዶቹን ከምስረታው ጊዜ ዓላማው ጋር ማነጻጸሩ በቂ ነው። በዓመታዊ ሪፖርቱ በግልጽ እንደተቀመጠው የISESP አመራር 75.880 (ሰባ አምስት ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ) ብር ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ከ1ኛ እስከ 3ኛ ለወጡ 60 ተማሪዎችና ለ20 ድሃ ተማሪዎች ማከፋፈሉን ገልጿል። ይህ ገንዘብ በዚህ ዓይንት መልክና ለዚህ ዓላማ እንዲከፋፈል ገንዘባቸውን በፈቃደኝንት ያዋጡት ኢሮቦች ተስማምተውበት የተደረገ ነው ብሎ ለመቀበል ይከብዳል። እንደኔ በግልጽ ሃሳባቸውን በጽሁፍ ባያቀርቡም የኔ ዓይንት ስሜትና አመለካከት ያለቸው ወገኖች በርካታ ሊሆኑ እንደምችሉም እገምታለሁ። ይህ ዓይነት አሳታፊነት የጎደሎው የተወሰኑ ሰዎች እንደፈለጉት የሚቀያይሩት ዓላማና አሰራር ዝም ተብሎ ከቀጠለ ወደ ትልቅ ሁሉንም አሳታፊ ማህበር መመስረት ቀርቶ ይህ የተጀመረው የተወሰኑ ተማሪዎች ለ4 ዓመት የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን እስከሚጨርሱ የማስቀጠል ፕሮጅክት መሳካቱም አጠራጣሪ ይሆናል። ስለሆነም የISESP አመራር ይህን ግድፈቱን በማስተካከል አስፈላጊ እርምት በወቅቱ እንዲያደረግ ግድፈቱን በወቅቱ ቢጠቆመው የተሻለ ነው በሚል እነሆ የአሰራር ግድፈት ሆኖ የተሰማኝን አቅርቤያለሁ።

### ለ. የISESP የቅድምያ አመራረጥ ግድፈት

በኢሮብ ወረዳ ዛሬ ሰፍኖ ያለውን ዘርፈ ብዙ የትምህርት ዝቅጠት ለመቅረፍ እኛ ኢሮቦች ምን ማድረግ አለብን? ለየተኛው ችግር ቅድሚያ ሰጥተን የተኛውን እናስከትል? የተገኘችውን ትንሽዋንም እንኳን ገንዘብ ምን ላይ ኢንቨስት እናድርግ? .....ወዘተ. በመሳሰሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ገና ሰፊና ጥልቅ ውይይት ያስፈልገናል። ይህን ውይይት በተገቢ ደረጃ መደረግ ቀርቶ ገና ሳይጀመር፣ ያሉት መሰረታዊ ችግሮች በሚገባ ተለይተው በቅደም ተከተል ሳይቀመጡ፣ ISESP ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ችግር አሁን በተማሪዎች ውስጥ ጠፍቶ ያለውን የትምህርት ፍላጎት እንደገና ለማነሳሳት፣ በተማሪዎች መካከል ፉክክር ለማበረታታት፣ ጎበዝ ተማሪዎችን መሸለም ነው የሚለውን እንደ ዋነኛ ችግር ወስዶ ከተገኘው ትንሽ ገንዘብ አብዛኛውን ለዚህ ተግባር አውሎታል። ለኔ ይህ የISESP ቅድሚያ አመራረጥና ከተገኘው ትንሽ ገንዘብ አብዛኛውን (75.880.00 ብር) ገንዘቡን ካዋጡት በሚገባ ሳይመክር ለዚህ ማዋሉ ትክክል አይመስለኝም። አሁን ያለፈ አልፏል፣ ለወደፊቱ ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ ግን ISESPም ሆነ ሁላችን ጉዳዩ የሚመለከትን ወገኖች መልስና መፍትሄ ልናገኝለት ይገባል። ይህ እንዳለ ሆኖ በእኔ በኩል ቅድሚያ ሰጥተን መፍትሄ ልንፈልግላቸው የሚገቡን መሰረታዊ ችግሮች ናቸው የምላቸውን ላስቀምጥ።

## VI. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ መሰረታዊ ችግሮች የተኞቹ ናቸው?

1. ብቃት ያላቸው አስተማሪዎች ለመፍጠር መስራት
2. በት/ቤቶች መሟላት ያለበቸው መጻህፍትና ሌሎች ቁሳቁሶች ለሟሟላት መጣር
3. የተማሪዎች አካላዊና ስነአእምሮአዊ ዝግጅት ለማሳደግ መስራት የሚሉት ከምንም በላይ ቅድሚያ ሰጥተን ለማቃለል ልንረባረብባቸው የሚገቡን ችግሮች ናቸው።

ስለሆነም በኢሮብ ወረዳ ሰፍኖ ያለውን የትምህርት ችግር ለመቅረፍ የሚሰራ ማህበር በፈለገው ስም ይቋቋም እነዚህን መሰረታዊ ችግሮችን እንደ ቅድሚያ አስቀምጦ ማንንም ሳያገል ለመስራት የተዘጋጀ መሆን አለበት እላለሁ።

በመጨረሻም ሁሉንም ኢሮቦች የሚከተሉትን ለማሳሰብ እወዳለሁ።

አንደኛ፣ ይህ ለወጣቶቻችን ተገቢ ትምህርት ሰጥቶ ትክክለኛ አቅጣጫ የማስያዝ ጉዳይ በቀጥታ ከወደፊት የኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልውና ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሁሉም በጥብቅ ሊያስብበትና ተገቢ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ሁሉም እንዲረባረብ በጥብቅ ለማሳስብ እወዳለሁ።

ሁለተኛ፣ እንደዚህ ዓይነት የወደፊት የብሄረሰባችንን ህልውና በቀጥታ የሚነኩ ችግሮች ለውይይት በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉም በውይይቱ መሳተፍ አለበት እላለሁ።

ሶስተኛ፣ ይህ ዓይነት ከባድና ውስብስብ ሁላችንም የሚነኩ ችግርን በፖለቲካ አመለካከት ተከፋፍለን ሳይሆን በኢሮብነታችን በጋራ በመመካከርና በመስራት ብቻ ልንፈታቸው እንደምንችል ሁሉም ሊያውቀው ይገባል።

አራተኛ፣ እኛው ኢሮቦች ለዚህ ዓይነት የጋራ ችግራችን በጋራ መቆምና መስራት ካቃተን መውቀስ ያለብን እኛው ራሳችንን እንጂ የሆነ ሌላ አካል መሆን እንደሌለበት በግልጽ መታወቅ አለበት። እኛው አንድ ሆነን በጋራ ችግራችን፣ ለምሳሌ የትምህርት ችግር፣ የድንበራችን ጉዳይ፣ ሻዕቢያ ደብዛቸውን ስላጠፋው ዜጎቻችን ጉዳይ...ወዘተ. በተመለከተ በአንድነት መቆም ብንችል በመንግስት ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ላይ ህግን ተመርኩዘን ከፍተኛ ተጽዕኖ ለማሳደር እንደምንችልም በግልጽ መታወቅ አለበት።

አምስተኛ፣ በየአከባቢው ያላችሁ የኢሮብ ምሁራን እስካሁን ከመረጣችሁት ዝምታ በመውጣት ትክክለኛ አቅጣጫን የማስያዝ ምሁራዊ ግዴታችሁን መወጣት መቻል አለባችሁ። ይህን ሳታደርጉ ብትቀሩ፣ ነገ በታሪክ እንደምትጠየቁም ማወቅ ያለባችሁ ይመስለኛል።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር!

በየነ ገብራይ ከደንማርክ

ለአስተያየት ሆነ ጥያቄ የሚከተለውን የኢመይል አድራሻ መጠቀም ይቻላል

beyene54@yahoo.com